የህዝብ መጓጓዣ አገልግሎት። በኪንግ ወረዳ ለመዘዋወር ጠቃሚ መረጃ

ይ ህ የጉዞ መረጃ በኪንግ ወረዳ እንደልብ መጓጓዝ ይችሉ ዘንድ እንዲረዳዎት ታስቦ በሶስት ተከታታይ ክፍሎች የቀረበው ቪድዮ በህትመት መልክ ተዘጋጅቶ ነው። የቪድዮ መረጃውን በኢንተርኔት (በይነ መረብ) አድራሻ፡ www.youtube.com/user/kcmobilitycoalition. ይመልከቱ። እነዚህ ቪድዮዎችና መረጃዎች በተለያዩ ቋንቋዎች በነጻ ተዘጋጅተዋል። ይደሰቱ!

በአውቶቡስ መጓዝ

በአውቶቡስ ፌርማታው ቢያንስ አምስት ደቂቃ አስቀድመው ይድረሱ። አውቶቡሱ ሲመጣ፣ ከአውቶቡሱ ፊትና ጉን ላይ የሚገኙትን የአውቶቡስ መድረሻ ምልክቶችን ይመልከቱ። ትክክለኛው አውቶቡስ መሆኑን ለማረጋገጥ ቁጥሩን ያመሳክሩ።

እንግሊዘኛ የማይናገሩ ከሆኑ፣ የመድረሻዎንና የመመለሻዎን አውቶቡስ ፌርማታ ቤተሰብዎ እንዲጽፍልዎት ያድርጉ። አውቶቡሱ ላይ ሲሳፈሩ ለሹፌሩ ያሳዩ።

የሚፈልጉት አውቶቡስ ሲመጣ፣ አውቶቡሱ ላይ መሳፈር እንደሚፈልጉ ሹፌሩ እንዲያውቅ እጅዎን አንስተው ምልክት ያድርጉ። አውቶቡሱ ውስጥ ከመግባትዎ በፊት ለመሳፈሪያ የሚከፍሉትን ያዘጋጁ።

አውቶቡሱ ውስጥ ከፊት የሚገኙት ወንበሮች ለአዛውንትና በአካል ለታጎሉ ሰዎች የተመደቡ መቀመጫዎች ናቸው። ሹፌሩን ማዳመጥና ማየት በሚችሉበት ቦታ ላይ ይቀመጡ።

እባክዎን ሌሎች ተሳፋሪዎች ወደ መቀመጫ ወንበሮቻቸው መተላለፍ እንዲችሉ መተላለፊያውን አይከልሉ። ሻንጣዎን እጅንዎ ላይ ወይም ከወንበር ሥር ያስቀምጡ።

ሁሉም የሜትሮና የሳውንድ ትራንዚት አውቶቡሶች የተሽከርካሪ ወንበሮች (ዊልቸር)፣ ስኩተር፣ ታጣፊ ምርኩዝ ወይም ከዘራ ለሚይዙ ሰዎችና ደረጃ ላይ መውጣት ለሚያቅታቸው ሰዎች ሊፍት(አሳንሱር) ወይም አግዳሚ መወጣጫ አላቸው። በሊፍት(አሳንሱር) ወይም በአግዳሚ መወጣጫ አውቶቡሱ ላይ መሳፈርና መውረድ የሚችሉት በመወጣጫ መሳፈር በሚችሉበት ፌርማታ ነው፣ ፌርማታውም ላይ የተሽከርካሪ ወንበር ምልክት ተለጥፏል። በሊፍት(አሳንሱር) ወይም በአግዳሚ መወጣጫ መሳፈር እንደሚፈልጉ ሹፌሩ እንዲያውቅ በዓይን ምልክት ያድርጉለት። ተሽከርካሪ ወንበር ላይ የተቀመጡ ከሆኑ፣ በሊፍት(አሳንሱሩ) ወይም አግዳሚ መወጣጫ ይሳፈሩና ለተሽከርካሪ ወንበር በተመደበው የአውቶቡሱ የፊት መቀመጫ ቦታ ይተላለፉ። ሹፌሩ በቀበቶ ወንበርዎን ያስርልዎታል።

መድረሻ ፊርማታዎ መቃረቡን ሲያውቁ፣ ከአውቶቡሱ ለመውረድ መፈለግዎን ሹፌሩ እንዲያውቅ ፊርማታዎ ለመድረስ ትንሽ ሲቀርዎት በአውቶቡሱ መስኮት አግዳሚያ የተዘረጋውን ምልክት መስጪያ ገመድ ሳብ ያድርጉት። አንዳንድ አውቶቡሶች ገመድ ሳይሆን ብጫ መስመር ምልክቶች ሊኖራቸው ይችላል። እባክዎን ከአውቶቡሱ ለመውረድ ከመነሳትዎ በፊት አውቶቡሱ እስኪቆም ድረስ ይጠብቁ። ይህ እንዳይወድቁ ይከላከላል።

በተሽከርካሪ ወንበር የሚጠቀሙ ከሆነ፣ በወንበሩ አካባቢ ካሉት ታጣፊ መቀመጫዎች ሥር የሚገኘውን ብጫ መስመር ደወል ይጫኑ። አውቶቡሱ ከቆመ በኋላ፣ ሹፌሩ የተሽከርካሪ ወንበርሩን ቀበቶ እስኪፈታ ድረስ ይጠብቁ።

King County METRO

SOUNDTRANSIT

ኪንግ ካውንቲ ሜትሮ እና ሳውንድ ትራንዚት ለአዛውንትና በአካል ለታጎሉ ሰዎች ስለ አውቶቡስ መሳፈር የነጻ ትምህርት ይሰጣሉ።
206-749-4242

hopelink
Helping People. Changing Lives.

ሆፕሊንክ በቡድን ለሚመጡ ሰዎች አውቶቡስ እንዴት እንደሚሳፈሩ የስልጠና ትምህርት ይሰጣል። የስልጠና ፕሮግራማቸው ራይድ አራውንድ ዘ ሳውንድ ተብሎ የሚጠራ ሲሆን አነስተኛ-ገቢ ላላቸው ግለሰቦች፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታቸው ውስን ለሆነ ሰዎችና ለአባት ጦረኞች የተዘጋጀ ነው። 425-943-6760

ልዩ አቀራረብና ቋንቋዎች

ጥያቄ ከቀረበ ይህ የጉዞ መረጃ ለተጠቃሚው በሚያመች መልኩ ተሻሽሎ በሚከተሉት ቋንቋዎች ሊዘጋጅ ይችላል፣

- እንግሊዝኛ
- ራሽያ
- አማርኛ
- ሶማሊ
- በርሜስ
- ስፓኒሽ
- ኔፓሊ
- ትግርኛ

ለበለጠ መረጃ አባኮዎን 425-943-6737 (ቮይስ) ወይም 711 (TTY ማዞሪያ) ይደውሉ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የስልክ ትርጉም አገልግሎት ይሰጣል።

ለበለጠ የመረጃ አገልግሎት

ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን እነዚህን ቁጥሮች ይደውሉ።

Sound Transit
1-800-201-4900

Metro
206-553-3000

እናመሠግናለን!

በከተማ አውቶቡሶችም ሆነ በሌላ የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎቶች በቅርቡ ተጠቃሚ ሆነው እንደምናገኝዎት ተስፋ እናደርጋለን።

King County
Mobility Coalition
425-943-6737

King County MOBILITY COALITION

የህዝብ ማመላለሻ መረጃ የኪንግ ወረዳ ክቦታ ቦታ መዘዋወር ህብረት ፕሮጀክት (the King County Mobility Coalition) ሲሆን ተል ዕኮው ህብረተሰቡ በኪንግ ወረዳ የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት የመጠቀም ልምድ እንዲያዳብር ማበረታታ ነው።ይህ መርሃ-ግብር (ፕሮጄክት) ዕውን ሊሆን የቻለው በ Bhutanese Community Resource Center, City of Kent, Coalition for Refugees from Burma, Hopelink, Jewish Family Service, King County Housing Authority, King County Metro, National Center for Senior Transportation, Salaam Urban Village Association, SeaMar Community Health Centers, Senior Services, Somali Community Services of Seattle, Sound Transit, UW Medicine-Harborview Medical Center, and Washington State Refugee Elder Grant.

የህዝብ መጓጓዣ አገልግሎት። በኪንግ ወረዳ ለመዘዋወር ጠቃሚ መረጃ

ይ ህ የጉዞ መረጃ በኪንግ ወረዳ እንደልብ መጓጓዝ ይችሉ ዘንድ እንዲረዳዎት ታስቦ በሶስት ተከታታይ ክፍሎች የቀረበው ቪድዮ በህትመት መልክ ተዘጋጅቶ ነው። የቪድዮ መረጃውን በኢንተርኔት (በይነ መረብ) አድራሻ፡ www.youtube.com/user/kcmobilitycoalition. ይመልከቱ። እነዚህ ቪድዮዎችና መረጃዎች በተለያዩ ቋንቋዎች በነጻ ተዘጋጅተዋል። ይደሰቱ!

ለአውቶቡስ ወይም ለላይት ሬይል ባቡር መሳፈሪያ ሂሳብ መክፈል

በሜትሮ አውቶቡስ፣ በሳውንድ ትራንዚት አውቶቡስ እና በሳውንድ ትራንዚት ላይት ሬይል ባቡር ለመጓዝ ጥሬ ገንዘብ (ካሽ) መክፈል ይችላሉ። በአውቶቡስ ለመጓዝ ጥሬ ገንዘብ የሚከፍሉ ከሆነ፣ ከሹፌሩ አጠገብ በሚገኘው ሂሳብ መክፈያ ሳጥን (ፌርቦክስ) ውስጥ ገንዘቡን ይጨምሩ። ትክክለኛውን የሂሳብ መጠን መጨመር ያስፈልግዎታል። ሹፌሮች ምንዛሪ ገንዘብ የላቸውም።

በላይት ሬይል ባቡር ለመጓዝ ጥሬ ገንዘብ የሚከፍሉ ከሆነ፣ በባቡሩ ጣቢያ ከሚገኘው ትኬት መሸጫ "ማሽን" ትኬቶቹን መግዛት ያስፈልግዎታል። ከተሳፈሩ በኋላ ትኬት መግዛት አይችሉም።

ወደሚሄዱበት አድራሻ ለመድረስ ከአንድ በላይ ሜትሮ አውቶቡስ የሚሳፈሩ ከሆነ፣ ለሁለተኛው አውቶቡስ ለመክፈል የመዛወሪያ ትኬት (ትራንስፈር) መጠቀም ይችላሉ። ለመጀመሪያው አውቶቡስ ሂሳብ ሲከፍሉ የመዛወሪያ ትኬት (ትራንስፈር) እንዲሰጥዎት ሹፌሩን ይጠይቁ። እንግሊዘኛ የማይናገሩ ከሆኑ፣ ቤተሰብዎ "Transfer Please" የሚል ጽሑፍ በብጣሽ ወረቀት ላይ እንዲጽፉልዎት አድርገው ሲሳፈሩ ለሹፌሩ ያሳዩ። በሚቀጥለው አውቶቡስ ላይ ሲሳፈሩ፣ ለሹፌሩ የመዛወሪያ ትኬቱን (ትራንስፈር) ያሳዩ።

የመዛወሪያ ትኬቶች የሚያገለግሉት ለሜትሮ አውቶቡሶች ብቻ ነው። ከሜትሮ አውቶቡሶች ወደ ሳውንድ ትራንዚት አውቶቡሶች ወይም ወደ ላይት ሬይል ባቡር ለመዛወር የመዛወሪያ ትኬቶችን መጠቀም አይችሉም።

ለመሳፈሪያ በ ORCA ካርድ የሚጠቀሙ ከሆነ፣ በአውቶቡስና በላይት ሬይል መጓዝ ቀላል ይሆናል። የ ORCA ካርዱን ከ 201 ሳውዝ ጃክሰን ስትሪት፣ ሲያትል፣ ከሜትሮ የባለጉዳዮች አገልግሎት ቢሮ ወይም ከላይት ሬይል ባቡር ጣቢያ ትኬት መሸጫ "ማሽን" መግዛት ይችላሉ። ደግሞ የ ORCA ካርዱ በኦንላየን www.orcacard.com ወይም በፖስታ እንዲደርስዎት 1-888-988-6722 በመደወል ማዘዝ ይችላሉ።

በ ORCA ካርዱ ላይ ገንዘብ ወይም ወርሐዊ መጓጓዣ ሂሳብ ካልጨመሩበት ሊያገልግል አይችልም። በኦንላየን፣ በፖስታ፣ ከአውቶቡስ ወይም ከላይት ሬይል ባቡር ጣቢያ ከሚገኙት "ማሽኖች"፣ ወይም ከብዙ የ ኪው ኤፍ ሲ፣ ሴፍዌይ እና ሳርስ ማርኬትፕሌስ ምግብ መደብሮች፣ ሂሳቡን በ ORCA ካርድዎ ላይ ይጨምሩ።

ለአውቶቡስ መሳፈሪያ በ ORCA ካርድ ለመክፈል፣ ሲሳፈሩ አውቶቡሱ ውስጥ በሚገኘው ሂሳብ አንባቢ መሣሪያ ላይ የ ORCA ካርዱን መታ መታ ያድርጉ። በ ORCA ካርድ ሂሳብ ሲከፍሉ፣ የመዛወሪያ ትኬት (ትራንስፈር) እንዲሰጥዎት ሹፌሩን መጠየቅ አያስፈልግዎትም።

ለላይት ሬይል ባቡር መሳፈሪያ በ ORCA ካርድ ለመክፈል፣ ከመሳፈርዎ በፊት በባቡሩ መድረክ ላይ በሚገኘው ቢጫ ሂሳብ አንባቢ መሣሪያ ላይ የ ORCA ካርዱን መታ መታ ያድርጉ። ደግሞም ከባቡሩ ሲወርዱ መሣሪያው ሂሳቡን እንዲያነብ ካርዱን መታ መታ ማድረግ እንዳለብዎት ያስታውሱ።

ዕድሜዎ 65 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ፣ የ ORCA ቅናሽ መሳፈሪያ ፈቃድ ቢኖርዎት በጣም ጥሩ ነው። ወደ ሜትሮ የባለጉዳይ አገልግሎት ቢሮ በመሄድ ወይም በፖስታ ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። የ ORCA ቅናሽ መሳፈሪያ ፈቃድ ካለዎት፣ የአውቶቡስና የላይት ሬይል ባቡር መሳፈሪያ ሂሳብ 75 ሳንቲም ብቻ ይሆናል። ዕድሜዎ ከ 65 ዓመት በታች ከሆነና በአካል የታሳሉ ከሆኑ፣ የ ORCA ቅናሽ መሳፈሪያ ፈቃድ እንዲሰጥዎት ማመልከቻ ሊያስገቡ ይችላሉ። አንድ የጤና ጥበቃ ባለሙያ ማመልከቻውን ከሞሉልዎት በኋላ፣ ባለፎቶ መታወቂያዎን ይዘው ወደ ሜትሮ የባለጉዳይ አገልግሎት ቢሮ መሄድ ያስፈልግዎታል።

ልዩ አቀራረብና ቋንቋዎች

ጥያቄ ከቀረበ ይህ የጉዞ መረጃ ለተጠቃሚው በሚያመች መልኩ ተሻሽሎ በሚከተሉት ቋንቋዎች ሊዘጋጅ ይችላል፣

- እንግሊዝኛ
- ራሽያ
- አማርኛ
- ሶማሊ
- በርሜስ
- ስፓኒሽ
- ኔፓሊ
- ትግርኛ

ለበለጠ መረጃ እባኮዎን 425-943-6737 (ቮይስ) ወይም 711 (TTY ማዞሪያ) ይደውሉ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የስልክ ትርጉም አገልግሎት ይሰጣል።

ለበለጠ የመረጃ አገልግሎት

ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን እነዚህን ቁጥሮች ይደውሉ።

Sound Transit
1-800-201-4900

Metro
206-553-3000

እናመሠግናለን!

በከተማ አውቶቡሶችም ሆነ በሌላ የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎቶች በቅርቡ ተጠቃሚ ሆነው እንደምናገኝዎት ተስፋ እናደርጋለን።

King County
Mobility Coalition
425-943-6737

King County MOBILITY COALITION

የህዝብ ማመላለሻ መረጃ የኪንግ ወረዳ ክቦታ ቦታ መዘዋወር ህብረት ፕሮጀክት (the King County Mobility Coalition) ሲሆን ተል ዕኮው ህብረተሰቡ በኪንግ ወረዳ የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት የመጠቀም ልምድ እንዲያዳብር ማበረታታ ነው።ይህ መርሃ-ግብር (ፕሮጄክት) ዕውን ሊሆን የቻለው በ Bhutanese Community Resource Center, City of Kent, Coalition for Refugees from Burma, Hopelink, Jewish Family Service, King County Housing Authority, King County Metro, National Center for Senior Transportation, Salaam Urban Village Association, SeaMar Community Health Centers, Senior Services, Somali Community Services of Seattle, Sound Transit, UW Medicine-Harborview Medical Center, and Washington State Refugee Elder Grant.

የህዝብ መጓጓዣ አገልግሎት። በኪንግ ወረዳ ለመዘዋወር ጠቃሚ መረጃ

ይ ህ የጉዞ መረጃ በኪንግ ወረዳ እንደልብ መጓጓዝ ይችሉ ዘንድ እንዲረዳዎት ታስቦ በሶስት ተከታታይ ክፍሎች የቀረበው ቪድዮ በህትመት መልክ ተዘጋጅቶ ነው። የቪድዮ መረጃውን በኢንተርኔት (በይነ መረብ) አድራሻ፡ www.youtube.com/user/kcmobilitycoalition. ይመልከቱ። እነዚህ ቪድዮዎችና መረጃዎች በተለያዩ ቋንቋዎች በነጻ ተዘጋጅተዋል። ይደሰቱ!

ሌሎች የመጓጓዣ አማራጮች

ሲንየር ሰርቪስስ ሃይድ ሸትልስ ዕድሜያቸው 55 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆናቸው አዛውንትና በማንኛውም ዕድሜ ላይ ሆነው በአካል ለታጎሉ ሰዎች በቫን የነጻ መጓጓዣ አገልግሎት ይሰጣል። ቫኖቹ ከሰኞ እስከ ዓርብ ባለው ጊዜ ውስጥ አገልግሎት የሚስጡ ሲሆን ተሳፋሪዎች በሠፈራቸው ውስጥ መሄድ ወደሚፈልጉባቸው ቦታዎች ያደርሷቸዋል። አገልግሎቱን የሚሰጡባቸው መኖሪያ ሠፈሮች፣ ሲያትል፣ ሬንተን፣ ቢርየን፣ ዲሞይን፣ ሾርላይን፣ እና ስኖኮልሚ ቫሌ ናቸው። 206-727-6262

ሲንየር ሰርቪስስ ቮለንቲር ትራንስፖርቴሽን ዕድሜያቸው 60 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆናቸውን አዛውንት ወደ ሐኪም ቀጠሮዎቻቸው በግል መኪና በነጻ የሚያደርስ የፈቃደኞች አገልግሎት መስጪያ ነው። መኪና ነጂዎቹ አዛውንቱን ቀጠሮ ቦታቸው ማድረስ ብቻ ሳይሆን እዚያው ጠብቀው በሰላም እቤታቸው ይመልሷቸዋል።
206-448-5740

ወደ ሐኪም ቀጠሮ የሚሄዱ ከሆኑ፣ የሆፕ ሊንክ ትራንስፖርቴሽን ዲቪዥን ሊረዳዎት ይችል ይሆናል። ሆፕሊንክ ለሜዲኬድ ታካሚዎች የአውቶቡስ ትኬቶችን፣ የጋዝ ካርዶችን፣ ለመኪና ማቆሚያ እርዳታን፣ ታክሲን፣ እና ሊፍት ያላቸው ቫኖችን የሚጨምር የመጓጓዣ አገልግሎት ያቀርባል።

ለስልክ ጥሪዎ እርዳታ የሚያደርጉ የቃል አስተርጓሚዎች ይኖራሉ።
1-800-923-7433

ሜትሮ አክሰስ ትራንስፖርቴሽን በአውቶቡስ እንዳይጓዙ የሚያግዳቸው የአካል መታጎል ላለባቸው ሰዎች በቫን ማመላለሻ አገልግሎት ይሰጣል። በቫኑ ከሌሎች ተሳፋሪዎች ጋር አብረው ይሳፈራሉ። በአውቶቡስ መጓዝ የማይችሉ መሆንዎ እንዲታወቅ የግለሰብ ግምገማንም የሚጨምር ማመልከቻ መሙላት ያስፈልግዎታል። 206-263-3113

ያለ አጋዥ ታክሲ ላይ መሳፈርና መውረድ ለሚያቅታቸው ሰዎች የተሽከርካሪ ወንበር (ዊልቸር) መሳፈሪያ ያላቸውን ታክሲዎች የሎካፕ ያቀርባል። እባክዎን ሲደውሉ የተሽከርካሪ ወንበር መሳፈሪያ ያላቸውን ታክሲዎች እንደሚፈልጉ ይንገሯቸው።

1-800-923-7433

በጉዞዎ መጨረሻ ላይ የቆጠረውን ሂሳብ ለታክሲ ነጂው ለመክፈል ታክሲ ስክሪፕ እንደ ገንዘብ ሆኖ ያገለግላል። የታክሲ መሳፈሪያ ሂሳቡን ግማሹን ዋጋ እንዲከፍሉ ያደርጋል፤ የ $10 ታክሲ መሣፈሪያ ሂሳብ $5 ብቻ ያስወጣል። የ ORCA ቅናሽ መሣፈሪያ ፈቃድ ካለዎት የታክሲ ስክሪፕ እንዲሰጥዎት ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። ከዚያም ከኪንግ ካውንቲ ሜትሮ በየወሩ ታክሲ ስክሪፕ መግዛት ይችላሉ።

Metro Customer Service: 206-553-3000

ልዩ አቀራረብና ቋንቋዎች

ጥያቄ ከቀረበ ይህ የጉዞ መረጃ ለተጠቃሚው በሚያመች መልኩ ተሻሽሎ በሚከተሉት ቋንቋዎች ሊዘጋጅ ይችላል፣

- እንግሊዝኛ
- አማርኛ
- በርሜስ
- ኔፓሊ
- ራሽያ
- ሶማሊ
- ስፓኒሽ
- ትግርኛ

ለበለጠ መረጃ እባኮዎን 425-943-6737 (ቮይስ) ወይም 711 (TTY ማዞሪያ) ይደውሉ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የስልክ ትርጉም አገልግሎት ይሰጣል።

ለበለጠ የመረጃ አገልግሎት

ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን እነዚህን ቁጥሮች ይደውሉ።

Sound Transit
1-800-201-4900

Metro
206-553-3000

እናመሠግናለን!

በከተማ አውቶቡሶችም ሆነ በሌላ የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎቶች በቅርቡ ተጠቃሚ ሆነው እንደምናገኝዎት ተስፋ እናደርጋለን።

King County
Mobility Coalition
425-943-6737

King County MOBILITY COALITION

የህዝብ ማመላለሻ መረጃ የኪንግ ወረዳ ክቦታ ቦታ መዘዋወር ህብረት ፕሮጀክት (the King County Mobility Coalition) ሲሆን ተል ዕኮው ህብረተሰቡ በኪንግ ወረዳ የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት የመጠቀም ልምድ እንዲያዳብር ማበረታታ ነው።ይህ መርሃ-ግብር (ፕሮጀክት) ዕውን ሊሆን የቻለው በ Bhutanese Community Resource Center, City of Kent, Coalition for Refugees from Burma, Hopelink, Jewish Family Service, King County Housing Authority, King County Metro, National Center for Senior Transportation, Salaam Urban Village Association, SeaMar Community Health Centers, Senior Services, Somali Community Services of Seattle, Sound Transit, UW Medicine-Harborview Medical Center, and Washington State Refugee Elder Grant.